በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. ገ/ሚ/ቁ/116

ቀን / Date 01/11/2017

ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

የፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር የሚወስን መመሪያ ቁጥር 1095/2017 በመ/ቤታችን ተዘጋጅቶ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በመ/ቤታችን ድህረ-ገጽ ሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ተጭኗል።

ስለዚህ መመሪያው በመ/ቤታችን ድህረ-ገፅ ከተጫነበት ሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲደረግ እያሳሰብን የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ ለሁሉም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በተቋማችሁ በኩል እንዲደርሳቸው ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለክቡር የፊስካል ጉዳዮች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ (ያለ አባሪ)
አዲስ አበባ

Letter/tw



መመሪያ ቁጥር 1095/2017

የፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ

ቁጥር 1095/2017

DIRECTIVE NO. 1095/2025

FEDERAL GOVERNMENT PROPERTY ADMINISTRATION DIRECTIVE



ሰኔ፣ 2017 ዓ.ም

July / 2025

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

መመሪያ ቁጥር 1095/2017
የፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ

የመንግስት ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት እና በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በማድረግ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኃላፊነታቸው ስር ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ ለማስቻል፤

የመንግሥት የንብረት የሚተዳደርበት ሥርዓት የሕይወት ዘመን ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን እና መልሶ መጠቀምን የሚያበረታታ፣ እንዲሁም የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌዴራል የመንግሥት ግዥና ንብረት አዋጅ ቁጥር 1333/2016 አንቀፅ 87 ንዑስ አንቀፅ 2 እና በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር (እንደተሻሻለ) 648/2001 አንቀፅ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ምዕራፍ አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1095/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

Directive No.1095/2025
Federal Government Property Admin istration Directive

Whereas the public property administration system must be transparent, efficient, effective, accountable, and supported by appropriate technology, in order to ensure that Public Bodies—within the scope of their responsibilities—diligently safeguard, utilize, and control government property, and, when such property is no longer required for service or is deemed unfit for use, dispose of it in a timely and appropriate manner;

Whereas it is necessary that the system for the administration of government property be based on a lifecycle management approach that promotes the reuse or recycling of assets, and it is essential that the administration of such property be undertaken in a manner that upholds the welfare of the public;

Now, therefore, the Ministry of Finance, pursuant to the authority vested in it under Article 87, Sub-Article 2 of the Federal Government Procurement and Property Administration Proclamation No. 1333/2016, and Article 75 of the Federal Government Financial Administration Proclamation No. 648/2001 (as amended), hereby issues this Directive.

CHAPTER ONE
GENERAL

1. Short Title

This Directive may be cited as the "**Federal Government Property Administration Directive No. 1095/2025**"

2. Definitions

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1) "ተሽከርካሪ" ማለት በመንገድ ላይ በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ወይም የሚጎተት ለሰውና ለዕቃ ማጓጓዣ የሚውል ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው።
2) "የእርጅና ቅናሽ" ማለት ንብረቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይሰጣል ተብሎ በሚገመትበት ዕድሜ ስርዓት ባለው አኳኋን የንብረቱን ዋጋ እንደ ወጪ እየተሰላ መቀነስ ነው።
3) "ክምችት" ማለት በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የተገዙ፣ የተመረቱ፣ በእርዳታ እና በስጦታ እንዲሁም ሌላ አግባብ ባለው ሁኔታ የተገኙ ንብረቶች ሆነው በመደበኛው የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ አገልግሎት ላይ እስከሚውሉ ድረስ በመጋዘን የተቀመጡ ፣ የሚቀመጡ እና ወጪ የሚሆኑ ቋሚ ዕቃ፣ አላቂ ዕቃ፣ እና ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሌሎች ዕቃዎች ማለት ሲሆን አገልግሎት ላይ ውለው በተለያየ መንገድ አገልግሎት የማይሰጡ ተብለው የተለዩ ወደ መጋዘን የሚመለሱ ዕቃዎችንም ያካትታል።
4) "አዋጅ" ማለት የፌዴራላዊ መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 ነው፤
5) **"የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ"** ማለት ተሿሚ ሆነው የፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤትን እንዲመሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ኃላፊዎች ናቸው።
6) **"የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊ"** ማለት በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ የሥራ ክፍልን የሚመራ ስራ አስፈፃሚ፣ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የሥራ አመራር ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ የሥራ ሂደት

Unless the context otherwise requires, for the purposes of this Directive:

1) **"Vehicle"** means any means of transportation that operates or is driven on roads by motor power and is used for the conveyance of persons or goods.
2) **"Depreciation"** means the process of systematically allocating the cost of a property over its estimated useful life, based on the premise that the asset will yield economic benefits during that period.
3) **"Inventory or Stock"** refers to properties procured, selected, received as aid or donation, or otherwise acquired by a public body, which are stored in a warehouse until deployed for regular operational use. This includes fixed assets, consumable goods, and other items requiring special handling, as well as those that, though temporarily out of service, are returned to the warehouse through various means.
4) **"Proclamation"** means the Ethiopian Federal Government Procurement and Property Administration Proclamation No. 1333/2024.
5) **"Head of Public Body"** means appointed officials who are responsible for leading a federal government institution.
6) **"Officials"** refers to executives who oversee organizational units within public bodies, including operational managers, office heads, chief executives, process leaders, administrative supervisors, and individuals holding equivalent positions of responsibility.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

መሪ፣ የመምሪያ ኃላፊ፣ እና በተመሳሳይ ደረጃ በሆነ የኃላፊነት መጠሪያ ቦታ ላይ የተመደበ ናው፣

7) "የተሽከርካሪ ጥገና" ማለት የተሽከርካሪውን ዕድሜ ለማራዘም የሚደረግ ቅድመ ብልሽትና እና ድህረ ብልሽት ጥገና ማድረግ ነው።

8) "ልኬት" ማለት አንድ ተሽከርካሪ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል ማወቅ ነው።

9) "ጋራዥ" ማለት ተሽከርካሪዎች ቅድመ ብልሽትና እና ድህረ ብልሽት ጥገና አገልግሎት የሚያገኙበት ቦታ ነው።

10) "ነዳጅ፣ ዘይት እና ቅባት መገልገያ እቃ" ማለት ነዳጅ፣ ዘይት እና ቅባት ለማከማቸት፣ ለማሰራጨት፣ ለመለካት እና ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ማሽነሪ እና ቁስ ነው።

11) "ኢ-ፍሊት ማኔጅመንት" ማለት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም የመንግስት ተሽከርካሪ መረጃን መዝግቦ መያዝ እና ማስተዳደር ነው።

12) በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋሉ በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

2. የተፈፃሚነት ወሰን

የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ሳይጨምር፣ ይህ መመሪያ አዋጁ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

4. የፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር ሥርዓት

7) **"Vehicle Maintenance"** means preventive and corrective servicing activities carried out to extend the operational lifespan of a vehicle.

8) **"Mileage"** refers to the measure of distance a vehicle can travel using one liter of fuel, expressed in kilometers per liter.

9) **"Garage"** means a facility where vehicles undergo preventive and corrective maintenance services.

10) **"Fuel, Oil, and Lubricant Dispensing Apparatus"** refers to the machinery and components used for the storage, distribution, measurement, and quality control of fuel, oil, and lubricants.

11) **"e-Fleet Management"** means the electronic recording, storage, and administration of government vehicle data using a digital system.

12) Terms and expressions defined in the Proclamation shall, when used in this Directive, carry the same meaning as assigned to them in the Proclamation.

3. Scope of application

This Directive shall apply to all Public Bodies to which the Proclamation is applicable, excluding Public Enterprises.

4. Federal Government Property Administration System

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

1) ማንኛውም በዚህ መመሪያ የተደነገጉት የመንግሥት የንብረት አስተዳደር ሥራዎች ሊከናወኑ የሚገባው ሚኒስቴሩ በዘረጋው ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት መሠረት መሆን አለበት::

2) በአዋጁ አንቀጽ 27 (4) በተደነገገው መሠረት ሚኒስቴሩ ለባለስልጣኑ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የመንግሥት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ የንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር የንብረት አስተዳደር ሥራውን ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ሥርዓት ለመፈፀም የባለስልጣኑን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው::

ምዕራፍ ሁለት
የመንግሥት ንብረቶች

5. ቋሚ ንብረቶች

ግዙፋዊ ሀልዎት ያለው፣ የተናጠል ዋጋው ብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ እና ከዚያ በላይ የሆነና ገቢ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ንብረት ቋሚ ንብረት ነው::

6. ልዩ ቋሚ ንብረት

ዋጋው ከብር 10,000 /አስር ሺህ ብር/ በታች ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ዕቃ ልዩ ቋሚ ንብረት ነው::

ምዕራፍ ሦስት
ተግባርና ኃላፊነት

7. የበላይ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት*

1. All government property administration activities governed by this Directive shall be executed by authorized personnel using the comprehensive and modern electronic government procurement and property administration system.

2. Pursuant to Article 27(4) of the Proclamation, where Federal Public Bodies are unable to implement the electronic property administration system, they shall obtain prior authorization from the Authority, based on the delegation granted to the Authority by the Ministry, to carry out property administration activities using a non-electronic system.

CHAPTER TWO
GOVERNMENT PROPERTIES

5. Fixed Asset

Any asset of significant durability, valued at 10,000 Ethiopian Birr (ten thousand Birr) or more, and capable of providing service for more than one year from the date of acquisition.

6. Special Fixed Asset

Any item with a value of less than 10,000 (Ten thousand Birr) Birr that is capable of providing service for more than one year.

CHAPTER THREE
DUTIES AND RESPONSIBILITIES

7. Duties and Responsibilities of the Head of the Public Body

የፌዴራል አስተዳደር አገልግሎት ሚኒስቴር 2

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

በአዋጁ የተሰጡ ተግባር እና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1) ለንብረት አስተዳደር ሥራ ክፍል በቂ እውቀት፣ የሥራ ልምድ እና መልካም ሥነ ምግባር ባላቸው የሰው ኃይል እንዲደራጅ እና እንዲመደቡ ማድረግ፤
2) የንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል ላይ የተመደቡ ወይም የሚመደቡ ሰራተኞች ሙያው በሚጠይቀው የትምህረት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ መሠረት የተመደቡ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3) የመንግሥት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጥ በመረሃ-ግብር የተደገፈ የአጠቃቀም የአያያዝ፣ የጥገና እና የአወጋገድ የውስጥ አሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣
4) በኦዲተሮች ወይም በሌላ አካል በመንግሥት ንብረት ላይ ጉድለት መኖሩ ሲረጋገጥ ንብረቱ በምርመራው መሠረት በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት ተሰልቶ በገንዘብ መከፈል ወይም ተመሳሳዩ እንዲተካ ማድረግ፣
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በተመሳሳይ ንብረት እንዲተካ ሲደረግ ቀደም ሲል ከነበረው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ አገልግሎት መስጠት የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፤
6) በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ ቁጥራቸው ከ3 ያላነሱ እና ከ 5 ያልበለጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፤

Pursuant to the duties and responsibilities assigned by the Proclamation, the head of the Public Body shall have the following specific duties and responsibilities:

1. To ensure that the Property Administration Unit is staffed with personnel possessing the requisite knowledge, work experience, and ethical integrity.
2. To confirm that personnel assigned or to be assigned to this unit are appointed based on the prescribed educational qualifications and relevant work experience.
3. To develop an internal system supported by a programme governing the use, supervision, maintenance, and disposal of government property, with a view to ensuring efficiency and cost-effectiveness in service delivery.
4. Where auditors or other competent authorities determine that there has been loss of or damage to government property, to ensure compensation is made in cash or in-kind based on the property's prevailing market value.
5. Where compensation is made in-kind pursuant to sub-article 4 of this Article, to ensure that the replacement property provides a level of service equivalent to that of the original asset.
6. In accordance with sub-article 4 of Article 5 of the Proclamation, to establish one or more Procurement and Disposal Committees as necessary for the approval of sale of assets to be disposed of, with a member not less than 3 and not more than 5, as necessary.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

7) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 መሠረት የሚቋቋመው ኮሚቴ የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንደ አስፈላጊነቱ የኮሚቴ አባላትን የአገልግሎት ዘመን ለሁለተኛ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፤

8) በንብረት ማስወገድ አፈፃፀም ሂደት ማንኛውም ሰው ቅሬታ ያቀረበ እንደሆነ የሚያቀርበውን ቅሬታ በማጣራት በጽሑፍ ምላሽ መስጠት፣

9) በንብረት አስተዳደር ለተመደበ የሥራ ኃላፊ፣ ሠራተኛ፣ ንብረት ሽያጭ ኮሜቴ አባላት፣ መንግሥት ያወጣውን የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕጎችና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች እንዲያውቁት እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓትን በተመለከተ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤

10) የመሥሪያ ቤቱን የንብረት አያያዝ፣ አጠቃቀም፣ ጥገና እና አወጋገድን አስመልክቶ የተዘጋጀውን ዓመታዊ ዕቅድ ማፅደቅና አፈጻፀሙን መከታተል፤

11) በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት ስር የሚገኙ ቋሚና አላቂ ንብረቶችን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ እንዲደረግ ማድረግ፤

12) እንደየፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤቱ የሥራ ባህሪ የጋራ አገልግሎት መጠቀሚያ ለሚሰጡ ንብረቶች የተለየ የውስጥ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት፤

13) የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቱ እንደሚያስተዳድረው ንብረት ዓይነትና ብዛት ከ3 (ሦስት) ያላነሱ አባላት ያሉት ኮሚቴ ወይም ከዚያ በላይ የንብረት ቆጠራ ኮሚቴ ማቋቋም፣

7. A committee established pursuant to sub-article 6 of this Article shall serve for a term of three years, and the head of the Public Body may, as deemed necessary, renew the term of the committee members once.

8. Where a person submits a complaint concerning the execution of a disposal, to ensure that a written response is provided following a thorough review of the complaint.

9. To ensure that designated officials, employees, Procurement and Disposal Committees, and other personnel involved in property management are made aware of and trained in the applicable government procurement and property administration laws and related documents.

10. To approve the annual plan of the Public Body relating to the supervision, utilization, maintenance, and disposal of property and follow-up its proper execution.

11. To ensure that a physical inventory count of both fixed and consumable assets under the responsibility of the Public Body is conducted at least once per fiscal year.

12. To develop an internal control and inspection system specifically applicable to assets that serve as common service utilities, in accordance with the operational characteristics of the Public Body.

13. To establish an Asset Inventory Committee comprising at least three members, or more as appropriate, based on the type and volume of property managed by the Public Body.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

14) የንብረት ቆጠራ ኮሚቴው ስለቆጠራ አፈጻጸሙ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ፤

15) መስሪያ ቤቱ የሚያስተዳድራቸው ቋሚ ፣ ልዩ ቋሚ እና አላቂ ንብረቶች ለታለመላቸው ዓላማ እየዋሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

16) የመንግሥት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢ ጥገና እና እንክብካቤ እየተደረገለት መሆኑን ማረጋገጥ፤

17) ለፕሮጀክት ሥራ አገልግሎት እንዲውሉ የተገዙ ቋሚና አላቂ ንብረቶች እንደማንኛውም የመንግስት ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤

18) የንብረት ማስወገድ ሥራው ከመስሪያ ቤቱ የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል አቅም በላይ በሚሆንበት ጊዜ በጊዜያዊነት ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ከ3 ያላነሱ አባላት ያሉት የንብረት አስወጋጅ እና የንብረት ዋጋ ገማች ኮሚቴ በማቋቋም እንዲወገድ ማድረግ፤

19) በንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል የንብረት አስተዳደር የተለያዩ ሥራዎች ራሳቸውን ችለው በተናጠል እንዲሰሩ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፤ እና

20) የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ በሽያጭ እንዲወገዱ የለያቸውን ተሽከርካሪዎች እዳና ተጠያቂነቶች ለይቶ ከተሟላ መረጃ ጋር ወደ ሚመለከተው አካል እንዲተላለፉ ማድረግ፤

8. የንብረት አስተዳደር ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ አንቀጽ 6 የተሰጡት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

14. To ensure that members of the Asset Inventory Committee receive adequate orientation regarding the conduct of inventory procedures.

15. To verify that fixed and consumable assets managed by the Public Body are utilized solely for their intended purposes.

16. To ensure that government property is maintained in good condition so as to promote its efficient and cost-effective use.

17. To ensure that fixed and consumable assets procured for project implementation are managed and used in accordance with the government property administration system.

18. Where the volume of disposal activities exceeds the capacity of the Property Management Unit, to establish an ad hoc Disposal and Asset Valuation Committee composed of at least three members drawn from different departments.

19. To ensure the implementation of a system that segregates duties within the Property Administration Unit.

20. To ensure that vehicles and other assets subject to disposal by the Public Body, along with their associated liabilities, are documented separately and submitted with full supporting information to the appropriate authority.

8. Duties and Responsibilities of the Property Administration Unit

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2
ሚኒስቴር

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

1) በአዋጁ እና ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ ሙያው በሚጠይቀው ክህሎት የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱን ንብረት ማስተዳደር፤

2) የተሟላ የንብረት አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት፣

3) በተቋሙ ውስጥ የሚገኙ የተቋሙ ያልሆኑ ንብረቶችን ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ ቁጥጥር እንዲደረግባቸውና ባለቤት እንዲኖራቸው ማድረግ፤

4) በንብረት ቆጠራ ሂደት ላይ አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለንብረት ቆጣሪ ኮሚቴው በአስረጅነት መሳተፍ።

5) በግዥ፣ በእርዳታ፣ በስጦታ፣ በውርስ፣ በማምረት እና በሌላ መንገድ የተገኘ ቋሚና አላቂ ዕቃን ፈትሾ፣ ቆጥሮ እና ለክቶ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ መረከብ፣

6) ክምችቱን በቢን ካርድ እና በክምችት ካርድ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክ የምዝገባ ዘዴ መዝግቦ መያዝ፣

7) በንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል የንብረት አስተዳደር ሥራ የንብረት ገቢና ወጪ እንዲሁም የንብረት ምዝገባና ቁጥጥር ሰራተኛ እና የመጋዘን ኃላፊ ሰራተኛ ተለያይተው በተናጠል እንዲሰሩ የተዘረጋውን ሥርዓት መተግበር፤

8) የመሥሪያ ቤቱን ቋሚ ንብረቶች በኤሌክትሮኒክ የአመዘጋገብ ዘዴ እና በቋሚ ዕቃ ካርድ እና በተጠቃሚ መቆጣጠሪያ ካርድ ላይ መዝግቦ መያዝ፣

9) የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም በቋሚ ዕቃ መመዝገቢያ ካርድ ለቋሚ ዕቃ የእርጅና ቅናሽ ማስላት፣

10) ለመሥሪያ ቤቱ አገልግሎት ወይም ጥቅም የማይሰጡ ንብረቶችን በመለየት እንዲወገዱ ለመንግስት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ለውሳኔ ማቅረብ፣

11) በሽያጭ እንዲወገዱ የተወሰነባቸውን ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ በማውጣት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፣ ጨረታውን

In addition to the responsibilities provided under Article 6 of the Proclamation, the Property Administration Unit shall have the following duties:

1. Administer the property of the Public Body in accordance with this Directive and in compliance with established professional standards.
2. Prepare a comprehensive property administration plan .
3. Identify any properties found within the Public Body's premises that do not belong to it, notify the appropriate authority for verification and control, and ensure that the rightful owner is identified.
4. Participate in the property inventory process and serve as the secretary of the inventory committee when required.
5. Record, inventory, and verify the accuracy of fixed and consumable items acquired through procurement, donation, inheritance, production, or other means.
6. Maintain inventory records using bin cards, stock cards, and electronic registration systems.
7. Establish and implement a system that ensures the segregation of duties within property administration functions for the receiving and issuing of property, registry and controller of property and the warehouse manager.
8. Electronically register the institution's fixed assets using Fixed Asset Register cards and User Control Cards.
9. Calculate depreciation for fixed assets using electronic systems within the Fixed Asset Register.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

እንዲወጣ ማድረግ፣ መገምገም አሸናፊና ተሸናፊውን በመለየት ለግዥና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ፤

12) ጨረታ ሠነዱ ላይ በተገለፀው ሁኔታ መሠረት የጨረታ ማስከበሪያውን የቆይታ ጊዜ መከታተል፣ አሸናፊው እንደታወቀም ለተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ እንዲመለስላቸው ማድረግ፣

13) በጨረታ ሰነዱ ላይ ለሚቀርብ ጥያቄና ማብራሪያ ይሠጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

14) ጨረታ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት በቀጥታ እንዲከፈት ያደርጋል። የውስጥ አዲት ተወካይ በሌላ ህግ እስካልተከለከለ ድረስ ወይም ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር በጨረታ አከፋፈት ስነ-ሥርዓት ላይ እንደገኝ ይጋብዛል፤

15) የተሸጡ ንብረቶችን በጨረታው ላሸነፉ ተጫራቾች ተገቢውን የአሰራር ሥርዓት በመከተል ያስረክባል፤

16) የሚወገዱ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የተሽከርካሪውን የህይወት ታሪክ የሚያሳይ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ፤

17) የንብረት ሰነዶችን መያዝ፣ መጠበቅ፣ ከሚመለከታቸው ሕጋዊ አካላት ማብራሪያ ሲጠየቅ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት፤

18) በዚህ መመሪያ በተገለፀው የገንዘብ ጣሪያ መሠረት በማዕከል ግዥን ለመፈጸምና ንብረትን ለማስወገድ በተቋቋመው የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት የሚወገዱትን ንብረቶች ለይቶ ለፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል።

19) የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቱን የንብረት አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድን አስመልክቶ የአፈፃፀም ሪፖርት ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ፤ መቅረብ፤

10. Identify properties that are no longer useful to the institution and submit recommendations for their disposal to the head of the Public Body.

11. Determine reserve prices for assets designated for disposal; prepare electronic bid documents; administer the tendering process; evaluate bids; and submit the results to the Procurement and Property Disposal Endorsement Committee.

12. Monitor the validity period of bid securities, ensure the return of bid securities to unsuccessful bidders, and verify compliance with the terms and conditions of the tender.

13. Provide clarifications or facilitate responses to inquiries regarding tender documents.

14. Conduct electronic tender openings in real-time, ensuring that representatives of the internal audit unit are present during the bid evaluation process to the extent it is not prohibited under other laws or it is not beyond force majeure.

15. Ensure that sold properties are properly handed over to successful bidders.

16. Disclose vehicle service history records to the relevant authorities when disposing of vehicles.

17. Safeguard all property-related documents, provide explanations when legally required, and respond to inquiries accordingly.

18. Notify the federal government body established to conduct central procurement ans property disposal regarding properties to disposed of through it based on the threshold set. .

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

20) በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ በቆጠራ ጊዜ የሦስተኛ ወገን ንብረቶች ከተገኙ ተለይተው እንዲመዘገቡና ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለመንግሰት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ፤

21) ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የሆኑ ንብረቶችን በወቅቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

22) የልዩ ቋሚ ንብረቶች በተጠቃሚ ካርድ በኤሌክትሮኒክ መመዝገቢያ ላይ በመመዝገብ በልዩ ሁኔታ መቆጣጠር፡ :

19. Submitting a performance report to the head of the public body regarding the use and management of the assets of the federal government office.

20. Report third-party properties discovered during inventory activities to the Head of the Public Body for appropriate resolution.

21. Distribute assets received into the property department to the user in a timely manner.

22. Track special fixed-assets by registering them electronically using User Control (UC) registration systems.

9. የትራንስፖርትና ስምሪት የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

1) የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቱን ተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ፤ ምደባ፣ የነዳጅ፣ የዘይትና የቅባት፤ ስምሪት፤ እና የጥገና ወጪን ዝርዝር በየወቅቱ በትክክል መዝግቦ መያዝ፤የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቱ ተሽከርካሪ ከተመደቡበት ዓላማ ውጪ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውሉ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፤

2) የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤቱን ተሽከርካሪ ተረክቦ እንዲያሽርከር የተፈቀደለት ሠራተኛ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠና አግባብነት ያለው የታደሰ የመንጃ ፈቃድ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

3) በተሽከርካሪዎቹ የግል ማህደር ውስጥ ከተመዘገበው መረጃ በመነሳት ተሽከርካሪዎች ወቅታቸው ጠብቆ የቅድመ ጥገና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤

9. Functions and Responsibilities of the Transport and Logistics Division

1. Maintain accurate and up-to-date records on the service history, classification, usage of fuel, oil, and lubricants, as well as maintenance costs of vehicles owned by the Federal Government. Ensure that such vehicles are not used for any purpose other than their officially designated function.

2. Verify that any employee authorized to operate Federal Government vehicles holds a valid and renewed driver's license issued by the appropriate authority.

3. Ensure that vehicles receive timely preventive maintenance based on the data recorded in their individual service files.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

4) የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ተሽከርካሪ የትራንስፖርት ባለሥልጣን በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ እንዲያገኙ ማደረግ፤

5) ሁሉም ተሽከርካሪዎች ተገቢው የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ የጎማ ማንሻ፤ መፍቻዎችና ሌሎች አስፈላጊ መሳሪያዎች እንዲኖራቸው ማድረግ፤

6) የኤሌክትሮኒክ ስርዓት በመጠቀም በመሥሪያ ቤቱ ይዞታ ስር የሚገኙትን ተሽከርካሪዎች ብዛት፤ ዓይነት፤ የሚገኙበትን ሁኔታ ማስረጃዎች በማጠናቀር የበጀት ዓመቱ እንደተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ማቅረብ፤

7) ከንብረት የሥራ ክፍል ጋር በመተባበር ለተሽከርካሪው የገቢ ሰነድ /ሞዴል 19/ በሚዘጋጅበት ወቅት በዚህ መመሪያ አባሪ 1 በመጠቀም የመረከቢያ ቅፅ ማዘጋጀት::

10. የአሽከርካሪ ተግባርና ኃላፊነት

1) የትራፊክ ደህንነት ደንብና መመሪያን አክብሮ ማሽከርከርና ተሽከርካሪውን ለተመደበለት ዓላማ ብቻ ማዋል፤

2) የትራንስፖርት ሕግና ደንብን በመተላለፍ በተሽከርካሪው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል እንዲቻል በኃላፊነት የተረከበውን ተሽከርካሪበጥንቃቄና በእንክብካቤ ማያዝ፤

3) ተሽከርካሪው ለእንቅስቃሴ ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል የሞተር ዘይት፤ የፍሬን ዘይት፤ የጎማ ሁኔታ እና ሌሎችም ስተሽከርካሪው

4. Ensure that Federal Government vehicles undergo annual technical inspections in accordance with the schedule issued by the Transport Authority.

5. Ensure that all vehicles are equipped with the required safety and utility equipment, including fire extinguishers, jacks, wrenches, and other essential tools.

6. Monitor the number, type, and condition of vehicles under the office's control using electronic systems. Collect and compile all relevant documentation and submit a report to the head of the Federal Government office within one month following the end of the fiscal year.

7. In coordination with the Property Administration Department, prepare a receipt form using Appendix 1 of this Directive when generating the vehicle disposal receiving document (Model 19).

10. Driver's Duties and Responsibilities

1. Operate vehicles in full compliance with traffic safety laws and regulations, and ensure that the vehicle is used exclusively for its designated official purpose.

2. Handle the assigned vehicle with due care and diligence to prevent any damage resulting from the violation of traffic laws and regulations.

3. Conduct regular checks on engine oil, brake fluid, tire condition, and other safety-critical

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ደህንነት ጋር በተያያዘ መፈተሽ የሚገባቸውን ጉዳዮች በየጊዜው መፈተሽ፤

4) በተሽከርካሪው ላይ ስርቆት ወይም አደጋ ከደረሰ በአካባቢው ለሚገኝ ፖሊስና ለመስሪያ ቤቱ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 2 ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ፤

5) የተረከበውን ተሽከርካሪ በጥንቃቄ እና በእንክብካቤ መያዝ እና ተሽከርካሪው ብልሽት ካጋጠመው ወይም ብልሽት መኖሩን የሚጠቁሙ ምልክቶችን ሲያይ ተሽከርካሪውን ከነችግሩ ከማሽከርከር መቆጠብና በወቅቱ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር 3 በተያያዘው ቅጽ መሠረት ሪፖርት ማድረግ፡፡፤

6) በኃላፊነት የተረከበውን ተሽከርካሪ ያለ ሕጋዊ ርክክብ በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ አሽከርካሪ አሳልፎ አለመስጠት፤

7) የተሽከርካሪው የቅድመ ብልሽት ጥገና ጊዜው ከመድረሱ በፊት በዚህ መመሪያ አባሪ 4 መሠረት አሽከርካሪው ለመስሪያ ቤቱ በጊዜው ማሳወቅ አለበት፤

ምዕራፍ አራት
የንብረት አስተዳደር ዕቅድ

11. የንብረት አስተዳደር ዕቅድ አዘገጃጀት

1) የፌደራል መንግስት ለመስሪያ ቤቱ በስሩ የሚያስተዳድራቸው ንብረቶችን አያያዝ፣ አጠቃቀም፣ ቅድመ ጥገና እና አወጋገድ አስመልክቶ በመርሃ ግብር የተደገፈ የንብረት አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት፤

components to ensure the vehicle is in proper working condition.

4. Immediately report any incident of theft or accident to the nearest police station or the appropriate department of the office, using the reporting format provided in Appendix No. 2 of this Directive.
5. Handle the assigned vehicle responsibly, and refrain from operating it in the event of a breakdown or signs of mechanical failure. Promptly report such issues to the appropriate department using the form attached to Appendix No. 3 of this Directive.
6. Under no circumstances shall the driver transfer or assign the use of the vehicle to another driver without formal legal authorization.
7. Notify the office in a timely manner, in accordance with Appendix No. 4 of this Directive, prior to the vehicle's scheduled preventive maintenance period.

CHAPTER FOUR
PROPERTY ADMINISTRATION PLAN

11. Preparation of Property Administration Plan

1) The Public Body shall prepare a property administration plan, supported by a strategy, that oversees the supervision, utilization, maintenance, and disposal of the properties under its control.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

2) የሚዘጋጀው የንብረት አስተዳደር ዕቅድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መሆን አለበት፤

ሀ/ በአዋጁ አንቀፅ 4 የተመለከቱትን የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መርሆችን ተግባራዊ ለማድረግ፤

ለ/ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ ፕሮግራም ለማሳካት እንዲያስችል ወቅቱን የጠበቀ የክምችት ፍላጎት ዕቅድ እንዲኖር ለማድረግ፡፡

ሐ/ አላስፈላጊ ክምችትንና የንብረት ብክነትን በመከላከል ወጪ ቆጣቢ አሰራርን ለማስፈን እና

መ/ በንብረት ርክክብ፣ አያያዝ፣ አጠቃቀም ጥገና እና አወጋገድ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን በቅድሚያ በመገንዘብ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ፡፡

12. የንብረት አስተዳደር ዕቅድ ይዘት

1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ መመሪያ የተገለጸው ዓላማ መሠረት በማድረግ የሚዘጋጀው ዕቅድ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡፡

ሀ/ የንብረት ክምችትና ስርጭት፤

ለ/ የንብረት ቆጠራና ቁጥጥር አፈፃፀም፤

ሐ/ የሚወገዱ ንብረቶች አይነት፣ ብዛት እና የሚወገዱበት መርሐ ግብር፤

መ/ የንብረት አስተዳደሩ የሚከተላቸውን ዝርዝር አሠራሮች (የንብረት አያያዝ እና አመዘጋገብ)፤

2) The prepared property administration plan shall be capable of achieving the following objectives:

a) To effectively implement the government property management principles outlined in Article 4 of the proclamation.

b) To ensure the institution has a timely and adequate maintenance demand plan that enables the achievement of its work program.

c) To prevent unnecessary maintenance and property damage by establishing a cost-effective management system.

d) To anticipate potential problems that may arise during the handling, supervision, utilization, maintenance, and disposal of properties, and to make appropriate preliminary preparations.

12. Content of the Property Administration plan

1) Public Bodies shall prepare a plan based on the purpose described in this directive, which shall include the following:

a) Property inventory and distribution;

b) Implementation of invemtory and control;

c) Types, quantities, and disposal procedures of properties to be disposed;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ሠ/ ቅድመ ብልሽትና እና ድህረ ብልሽት ጥገና መርሐ ግብር፣ እና

ረ/ ሌሎች እንደ መሥሪያ ቤቱ ባህሪ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን፡፡

2) የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል የንብረት አስተዳደር ዕቅድን በሚያዘጋጅበት ወቅት የዓመታዊ ቆጠራ ሪፖርትን፣ የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝርን፣ የዓመታዊ ቆጠራ ክምችት ሪፖርቶችን፣ የንብረቱ ተጠቃሚ የሥራ ክፍል ፍላጎት እና የሚቀርቡ ጥያቄዎችን፣ እና ሌሎች ግብዓቶችን መሠረት ማድረግ አለበት፡፡

3) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ለንብረት አስተዳደር ዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት የተጠቀመባቸውን ዋና ዋና መረጃዎች እና ሌሎች የንብረት ዕቅዱን ለተጠቃሚ ግልፅ መሆን አለባቸው ተብለው የሚታመንባቸውን መረጃዎች ከዕቅዱ ጋር በአባሪነት ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

13. የንብረት አስተዳደር ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ

1) የንብረት አስተዳደር ሥራ ክፍል ያዘጋጀውን ዓመታዊ የንብረት ዕቅድ ለመንግስት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ማፀደቅ አለበት፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የንብረት አስተዳደር ዕቅዱን ለማሻሻ የሚወገድ ንብረት አጽዳቂ ኮሚቴ ለአስተያየት መላክ አለበት፡፡ ኮሚቴው

d) Detailed procedures to be followed in property administration (property handling and registration);

e) Property maintenance and preventive maintenance procedures; and

f) Other issues relevant to the nature and focus of the Public Body.

2) When the Property Administratio Unit prepares the property administration plan , annual inventory report, list of properties to be disposed, annual inventory verification reports, user department's demand and requests, and other relevant inputs should be taken into consideration.

3) A Public Body shall maintain the main data and other information used in preparing the property administration plan with the plan itself, ensuring that the information is clear, reliable, and accessible to users.

13. Approval and Amendment of the Property Administration plan

1) The Property Management Unit must submit the annual property administration plan it has prepared to the Head of the public body for approval.

2) Once the plan referred to in sub-article 1 of this article is approved, the Head of the public body must send the property administration plan to the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ይህን ዕቅድ በመመርመር አስተያየቱን ለፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይሰጣል።

3) የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የንብረት አስተዳደር ሂደት በፀደቀው የንብረት ዕቅድ መሠረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን መከታተል አለበት፤

4) በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የፀደቀው ዓመታዊ የንብረት አስተዳደር እቅድ በአዋጁ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ለአፈፃፀም በመሥሪያ ቤቱ ለሚገኙ ሥራው ለሚመለከታቸው ሥራ ክፍሎች መድረስ አለበት።

5) የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲታመንበት የንብረት እቅዱን ሊያሻሽል ይችላል፤

6) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) የተሻሻለው የንብረት ዕቅድ የመጀመሪያው ዕቅድ ለተላከላቸው በመሥሪያ ቤቱ ለሚገኙ የሥራ ክፍሎች መድረስ አለበት።

ምዕራፍ አምስት
የክምችት አስተዳደር

14. የክምችት አስተዳደር ሥርዓት

1) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት የንብረት አስተዳደር ሥርዓትን በሚያከናውንበት ወቅት በኤሌክትሮኒክ የንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ መሠረት መሆን አለበት።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ተግባራዊ በማይሆንበት

Procurement and Property Disposal Committee for review and comments. The committee shall review the plan and provide its feedback to the Head of the public body.

3) Head of public body must establish a system of procedures to ensure that the property administration process is conducted in accordance with the approved plan and monitor its implementation.

4) The annual property administration plan , which will be approved by the head of the Public Body shall be communicated to the relevant units within the Public Body in accordance with Article 18, sub-article 1 of the Proclamation.

5) Public Bodies may amend their property administration plan s when necessary and when approved by the head of the Public Body.

6) The amended property administration plan referred to in sub-article 4 of this article shall be communicated to the relevant units within the Public Body.

CHAPTER FIVE
STOCK MANAGEMENT

14. Stock Management System

1. Public Bodies shall implement the property management system, based on the electronic property management system.
2. Without prejudice to sub-article 1 of this article, when the electronic system is not operational, Public Bodies shall ensure that there is adequate

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ወቅት የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ በሠራተኞች መካከል በቂ የስራ ክፍፍል መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡

ሀ/ ንብረት ገቢ ሲደረግና ወጪ ሲደረግ በተገቢው ሠነድ መሠራቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት፣

ለ/ ክምችት የመረከብ ፣ ወጪ የማድረግ እና በቢን ካርድ የማቀናነስ ኃላፊነት፣ እና

ሐ/ ክምችት በስቶክ ካርድ የመመዝገብ እና የማቀናነስ ተግባራት መነጣጣል አለባቸው።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ከኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ውጪ የተደረጉ ጉዳዮች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ በሚሰራበት ወቅት ሁሉንም መረጃዎች ወደ ሥርዓቱ ማስገባት አለባቸው።

15. የክምችት ቁጥጥር ሥርዓት

1) የክምችት ቁጥጥር ሥርዓት በእያንንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መዘርጋት ያለበት ሲሆን በክምችት የሚቀመጡ ዕቃዎች ለጤና አደገኞች ወይም ባላቸው ከፍተኛ ዋጋና በቀላሉ የመንቀሳቀስ ባህሪ ምክንያት ለስርቆት የሚጋለጡ ናቸው ተብሎ ሲታመን ልዩ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

2) በፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚደረገው ቁጥጥር ሥርዓት የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎችን ያገናዘበ መሆን አለበት፡-

ሀ/ የክምችት ቁጥጥር አስተማማኝ፣ ተገቢና መሠረታዊ የክምችት ሠነዶችን/ ቢንካርድ እና ስቶክ ካርድ/ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት።

ለ/ የንብረት ገቢ እና ወጪ ማድረጊያ ሰነዶች በኤሌክትሮኒክ አሰራር ስርኣት መሰረት ጥብቅ ቁጥጥር መደረግ አለበት።

division of labor among employees responsible for the following tasks:

a) Entry and issuing of property and preparation of appropriate documentation;

b) Responsible for receiving, issuing, and balancing inventory on a bin card, and

c) Recording inventory in stock cards and conducting reconciliation activities.

3. Notwithstanding sub-article 2 of this article, all information related to activities carried out outside the electronic system shall be entered into the electronic system once it becomes operational.

15. Stock Control System

1) Each Public Body establish an inventory control system. Special control is required for items stored in inventory that are considered health hazards, high in value, or easily movable and thus prone to theft.

2) The inventory control system implemented by the Public Body must incorporate the following fundamental principles:

a) The inventory control shall be reliable, appropriate, and based on fundamental inventory documents such as bin cards and stock cards.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ሐ/ ከላይ በፊደል ተራ "ለ" ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ላገለገሉ ንብረቶች የገቢ እና የወጪ ሠነድ መለየት አለበት፤

መ/ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ሰነዶች ንብረት ገቢ ወይም ወጪ ከተደረገባቸው በኋላ በዋ ዋና የክምችት ሠነድ በኤሌክትሮኒክ ስርዓት ዘዴ መቀናነስ አለባቸው፤

ሠ/ አዲስ የተረከቧቸውን፣ አገልግሎት ሰጥተው የተመለሱ እና የሚወገዱ ንብረቶችን ለይተው ማስቀመጥ አለባቸው፤

ረ/ የንብረት መጉደል ወይም መጭበርበር ተከስቷል የሚል ጥርጣሬ ሲኖር ንብረቱን ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ወጪ ማድረግን፣ ጥቅም ላይ መዋልንና አግባብ ያለው ሆኖ ሲገኝ እስከ ማስወገድ ድረስ ያለውን ሂደት ወደ ኋላ ሄዶ ማየትና የታተሙ ሰነዶች ቁጥራቸው ተከታታይና ይዘታቸው ያልተደለዘ ወይም ለውጥ ያልተደረገባቸው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

3) ቤተመፃህፍት ያላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የመፃህፍቱን አጠቃቀም ትውስት እና የተጠቃሚዎችን ግዴታ ባካተተ መልኩ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት አለባቸው።

16. መሠረታዊ የክምችት ሰነዶችን ስለመያዝ

1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የክምችት መረጃ መያዝና ማስተዳደር አለባቸው።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ‹1› የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ለባለስልጣኑ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የክምችት መረጃቸውን በተለየ ሁኔታ ለመያዝ አስፈላጊ

b) Documents related to property receipts and issuance shall be closely monitored through the electronic system.

c) Without prejudice to sub-Article 2 (b) of this Article, documents for received and issued properties shall be clearly distinguished.

d) After property receipt or issuing, the main stock documents shall be electronically reconciled.

e) Newly received, serviced and returned, and items to be disposed of shall be separately recorded and maintained.

f) In cases where property damage or loss is suspected, the process of expenditure, utilization, and proper handling shall be traceable from the date of receipt until disposal. The records must be sequential, intact, and free from unauthorized alterations.

3) Public Bodies with warehouses must establish an internal control system that includes the usage reconciliation of the warehouse and the obligations of the users.

16. Keeping Basic Inventory Documents

1) Public Bodies shall keep and manage inventory data using the electronic system.

2) Without prejudice to sub-Article 1 of this article, if necessary, Public Bodies may keep their inventory data separately in a distinct manner

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ሆኖ ሲገኝ ለባለስልጣኑ ጥያቄ በማቅረብ ሲፈቀድ መረጃውን በተለየ ሁኔታ መዝግበው መያዝ ይችላሉ፡ ፡

17. ክምችት ስለመቀበል

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎች ከማናቸውም ምንጭ ንብረቶችን ለክምችት ሲቀበሉ በሚከተሉት ላይ ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡ ፡

1) ከሚመለከተው የሥራ ክፍል ዕቃውን ለመረከብ የሚያስችል በፅሁፍ የተሰጠ ትዕዛዝ መኖሩን፣
2) የመጋዘን ቤት ኃላፊው የዕቃውን ትክክለኛነት ከተሰጠው ትዕዛዝ እና ከዕቃው ዝርዝር መግለጫ ጋር በማመሳከር ወይም ባለሙያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሙያ በጽሁፍ ማረጋገጫ ማግኘት፣
3) ክምችቱ የመጣው ከመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች ወይም ክምችቱን ከሚመልሱ የመሥሪያ ቤቱ አባላት ሲሆን ዕቃው ወጪ ከተደረገበት ሰነድ ጋር ማመሳከር፣
4) በፌደራል መንግሰት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር፣ የ ፌደራል መንግስት ለመስሪያ ቤቱ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከስድስት ወር በላይ ለትምህርት ወደ ውጪ ሀገር በሚሄዱበት ጊዜ ከመስሪያ ቤቱ ለሥራ ወጭ አድርጎ ሲጠቀምበት የነበረውን ንብረት በሙሉ ለመሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡
5) የኤሌክትሮኒክ የመረጃ ስርዓቶችን በመጠቀም ንብረቱን በተቀበለበት ዕለት መመዝገብ፣

upon request and approval by the Authority based on the power delegated to the Authority by the Ministry.

17. Receiving of a Stock

When Public Bodies' property administration units receive inventory from any source, they shall ensure the following:

1) There is a written authorization that allows the receiving unit to accept the goods.
2) The warehouse manager verifies the accuracy of the goods against the authorization and the detailed description of the items, or, if necessary, obtains a written confirmation from relevant expert.
3) The recipient shall be either a unit or a member of the unit authorized to receive the property, and shall be reconciled with the document evidencing the item to be issued.
4) Unless explicitly authorized by the head of the Public Body under special circumstances, any employee or official of the Public Body who is departing for training abroad for a period exceeding six months shall be required to return all government property assigned to them.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

6) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ መስሪያ ቤቱ ገቢ የሚሆኑ ንብረቶች መስሪያ ቤቱ የንብረት ሥራ ክፍል ተረጋግጦ ከመስሪያ ቤቱ መጋዘን ውጪ ገቢ የሚደረጉበትን ቦታ የፌደራል መንግሰት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

7) የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል ከተለያየ ምንጭ የተገኙ ንብረቶችን ገቢ ሲያደርጉ ስለትክክለኛነታቸው በአካል አረጋግጦ መረከብ አለበት፡፡

8) አገልግሎት ሰጥተው ከተጠቃሚ ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች በፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤቱ ላገለገሉ ንብረቶች ተብሎ በተዘጋጀው የተመላሽ ሰነድ ገቢ መደረግ አለባቸው፡፡

9) ከአንድ በላይ መጋዘን ያላቸው የፌደራል መንግሥት መ/ቤቶች ከዋናው መጋዘን ውጭ ገቢ ሲያደርጉ በዋናው መጋዘን ታውቆ እና ተገቢውን የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት እና ለመስሪያ ቤቱ ንብረት አስተዳደር ክፍል ሪፖርት በማድረግ መሆን አለበት፡
:

18. ንብረት ከመጋዘን የማውጣት ሥርዓት

1) ንብረት ከመጋዘን ሲወጣ መጀመሪያ የገባው መጀመሪያ ይወጣል የሚለውን የሂሣብ አሠራር ሥርዓት ተከትሎ ነው፣

ሀ/ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍል ኃላፊ ንብረት ከመጋዘን ሲወጣ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ሥርዓትን በመጠቀም ተገቢውን የወጪ ቀሪ መሰራቱን እና ለአያንዳንዱ ሠራተኛ የተሰጠው

5) The Property shall be recorded on the day it is received using the electronic data management system.

6) If necessary, the head of the Public Body may allow a place where the receipt and issuance of the properties to be conducted at the warehouse upon a verification of the property administration unit of the Public Body.

7) The property administration unit must physically verify and accept inventory received from different sources to ensure its accuracy.

8) Returned properties from users shall be recorded on the appropriate form prepared for this purpose.

9) Public Bodies with multiple warehouses must ensure that recorded by receiving document outside the main warehouse is known to the main warehouse, and a proper control system is established along with reporting to the property administration unit.

18. Property Issuance System

1. When property is issued from inventory, the first item received is the first to be issued following the First In First Out (FIFO) accounting method:

   a. The head of the department responsible for government property administration shall ensure that appropriate issuing records are maintained in the electronic system upon issuance of assets from the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

warehouse, and that the assets assigned to each employee are properly recorded.

b. When user departments or employees, including the head of the government office, require assets for official use, they shall complete an issue request form appropriately and submit it electronically to the department responsible for asset management after approval by the head of the respective department or office.

c. The asset administration unit shall verify the availability of the requested assets, either through the electronic system or physical stock, and submit the verified request to the head of the relevant government office for approval.

d. The issuance of the requested assets shall be processed electronically and acknowledged with the recipient's signature.

e. When used assets are returned by the user, the corresponding issuing document shall be accounted for using the appropriate asset expense documentation or electronic system.

f. Federal public body shall not utilize government assets unless the assets have been duly accounted for as receiving and issuing in accordance with applicable procedures.

የንብረት ዝርዝር ተመዝግቦ መያዙን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ/ የመንግስት መስሪያ ቤቱን ኃላፊ ጨምሮ ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ወይም ሠራተኞች ለሥራ የሚያስፈልጓቸውን ንብረቶች ወጪ ለማድረግ በሚፈልጉበት ወቅት የዕቃ መጠየቂያ ቅፅ በተገቢው ሁኔታ በመሙላትና በሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤቱ ኃላፊ ተረጋግጦ የንብረት አስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውን የሥራ ክፍል በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ታግዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

ሐ/ ንብረቱን የሚያስተዳድረው የሥራ ክፍል በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ወይም በንብረት ወጪ መጠየቂያ ወይም የተጠየቁት ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ያሉ መሆናቸውን በማጣራት በሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤቱ ኃላፊ በማቅረብ ያስወስናል፣

መ/ ወጪ እንዲሆን የተጠየቀው ንብረት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ተሞልቶና በተረካቢው ተፈርሞ ወጪ መደረግ አለበት፡፡

ሠ/ ያገለገሉ ንብረቶች መልሰው ለተጠቃሚ ወጪ በሚደረጉበት ወቅት በመስሪያ ቤቱ ላገለገሉ ንብረቶች በተገቢው ንብረት ወጪ ሰነድ ወይም በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ወጪ መደረግ አለባቸው፣

ረ/ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የመንግሥት ንብረትን በተገቢው መንገድ ገቢ እና ወጪ ሳይሆኑ የአገልግሎት ላይ ማዋል የለባቸውም፣

የንብረት አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ሰ/ ከላይ በፊደል ተራ "ረ" የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባስገዳጅ ሁኔታ የንብረት ገቢ እና ወጪ ሥርዓቶችን መከተል የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የመንግስት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፣

ሸ/ ለመሥሪያ ቤቱ የጋራ አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶች ስራው በሚመለከተው የሥራ ክፍል በሚወክለው ሰራተኛ ወጪ ሆነው ቁጥጥርና ክትትላቸውን በተመለከተ የጋራ ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲሆን የመንግስት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የአሰራር ሥርዓትን ይዘረጋል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ቀድመው የሚበላሹ ወይም የሚያረጁ ዕቃዎችን ወጪ የማድረግ ሂደትን በተመለከተ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ ኬሚካሎች፣ መድሀኒቶች፣ ምግቦችን እና ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ንብረቶች ሲያጋጥሙ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ንብረቶችን አስቀድሞ ወጪ በማድረግ በማድረግ ስራ ላይ እንዲውሉ መደረግ አለበት።

19. በተጠቃሚዎች መካከል የሚደረግ የንብረት ዝውውር

1) ሁኔታ ካላስገደደ በስተቀር የመንግሥት መስሪያ ቤቱ በተጠቃሚ ስር የሚገኙ ንብረቶችን በአካል ወደ መጋዘን መመለስ ሳያስፈልግ ከአንድ ተጠቃሚ ወደ ሌላ ማስተላለፍ ይቻላል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የንብረት ዝውውር ሲፈጸም የንብረቱ አስረካቢ እና ተረካቢ

g. Notwithstanding the provisions of subparagraph (f), where it is found that compliance with the standard asset receiving and issuing procedures is not feasible due to compelling circumstances, the head of the government office shall issue a formal decision authorizing an exception.

h. The head of the government office shall establish a procedural system whereby assets provided for common services are supervised and monitored by an employee designated by the relevant department, under a joint responsibility framework.

2. Notwithstnding sub-Article 1 of this Article, for perishable items such as chemicals, medicines, food, and similar items with a short service life, the issuance process shall follow the First Expiry First Out (FEFO) principle to ensure timely usage.

19. Property Transfer Among Users

1. Except in cases where conditions prohibit it, Public Body properties assigned to users may be transferred directly from one user to another without the need to return the property physically to the warehouse.

2. When such property transfer occurs as described in sub-article 1 of this article, both the transferor and the transferee must notify the property

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ንብረቱን ለሚያስተዳድረው የሥራ ክፍል ማሳወቅ አለባቸው::

20. የክምችት ቆጠራ አፈፃፀም

1) የክምችት ቆጠራ መደረግ ያለበት የንብረት ሰነዶችና ንብረቱን ከሚይዝ ሠራተኛ እና ኃላፊ ውጭ በሆነ አካል መሆን አለበት፣

2) የክምችት ቆጠራ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መካሄድ አለበት:: ሆኖም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የንብረት ጉድለት ሪፖርት ሲቀርብለት ወይም አዲስ የመጋዘን ሠራተኞች ሲመደቡ እና እንደንብረቱ ባህሪ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ የክምችት ቆጠራ መካሄድ መቆጠር አለበት ብሎ ሲያምን ቆጠራውን ሊያካሂድ ይችላል፣

3) የክምችት አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍል ኃላፊ የንብረት ቆጣሪ ኮሚቴው አባል ባይሆንም የክምችት ቆጠራ ሥራን ለማቀላጠፍ በአስረጂነት እና በአስቆጣሪነት መገኘት አለበት፣

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የንብረት ቆጣሪ ኮሚቴው የመስሪያ ቤቱን የንብረት ዓመታዊ ቆጠራ ፣ እንዳስፈላጊነቱ ድንገተኛ ቆጠራ እና አጠቃላይ ቆጠራ ያደርጋል፣

5) የንብረት አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍል ኃላፊ ኮሚቴው ቆጠራውን ለማካሄድ



management unit responsible for managing the property.

20. Execution of Inventory Counting

1. The inventory counting must be conducted by personnel and officials who are external to the custody and responsibility of the property being counted.

2. Inventory counting must be conducted at least once a year. However, the Public Body may conduct more frequent inventory counts during the submission of property loss reports, the appointment of new inventory staff, or when the nature of the property requires it.

3. The head of the unit responsible for property administration, even if he is not a member of the inventory committee, must be present to provide explanation ans serve as owner in the inventory counting process.

4. Without prejudice to the provisions of Sub-Article 3 of this Article, the Committee shall, in accordance with the decision of the Head, conduct an annual inventory of the Office's assets, as well as emergency or general inventories as deemed necessary.

5. The head of the unit responsible for property management must ensure that the committee has the necessary conditions and resources to effectively conduct the inventory counting.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

እንዲችል የሚረዳ የተሟላ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፣

6) ኮሚቴው ከቆጠራ በኋላና በየዕለቱ ስለተቆጠረው ንብረት ካስቆጣሪው ጋር የመተማመኛ ፊርማ መፈራረም አለበት፣

7) የቆጠራ ኮሚቴው እና አስቆጣሪው የቆጠራ ስራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ መጋዘኑን በጋራ የማሸግና የመክፈት ኃላፊነት አለባቸው፣

21. በክምችት ቆጠራ ላይ ሪፖርት ስለማቅረብ እና በተገኙ ልዩነቶች ላይ ምርመራ ስለማካሄድ

1) የክምችት ቆጠራውን የሚያካሂደው ኮሚቴ የቆጠራውን ዝርዝር ሪፖርት ለመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊው እና ለንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል ማቅረብ አለበት፣

2) የክምችት ቆጠራው ሪፖርት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የተመዘገበው ወይም በዕቃ መቀበያ ሰነድ፣ በክምችት መጠየቂያ እና ማውጫ ሰነድ መካከል የታዩትን ማናቸውም ልዩነቶች በዝርዝር እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች ለተቋሙ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተለይተው በሪፖርቱ መግለፅ አለበት።

3) በክምችት ወቅት ያጋጠመ ጉድለት ከተጣራና ውሳኔ ካገኘ በኋላ በዚህ መመሪያ መሠረት የጠፋው ንብረት እንዲተካ መደረግ አለበት።

22. የክምችት መጠንን ስለመቆጣጠር

1) የክምችት አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍል ለመደበኛ ሥራ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልግ የክምችት ፍላጎትን፣ የታዘዘ ዕቃን መጋዘን ለመድረስ

6. After the inventory counting, the committee and the inventory taker must jointly sign an acknowledgment form confirming the counted property.

7. The inventory committee and the inventory taker share joint responsibility for safeguarding and properly handling the inventory until the counting process is completed.

21. Reporting on Inventory Counting and Investigation of Discrepancies

1. The committee conducting the inventory count shall submit a detailed inventory report to the Head of the public body and property administration unit.
2. The inventory count report must detail any discrepancies found between the electronic system records or the receiving documents, stock requisitions, and stock issue documents. It shall also clearly identify any properties that are not available for service to the institution, specifying the reasons for such cases.
3. If any loss or damage is detected during the inventory count and a decision has been made, the lost property shall be accounted for and shall be replaced in accordance with this directive.

22. Stock Control

1. The unit responsible for property management shall maintain an adequate quantity of inventory to meet the stock demands required for the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

የሚፈጅውን ጊዜ፣ የመጋዘኑ የመያዝ አቅም እና የግዥ ትዕዛዙን ለመፈፀም የሚያስፈልገውን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት በየጊዜው የሚያስፈልግ ክምችትን በበቂ መጠን መያዝ አለበት።

2) የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎችና መድሃኒቶች ሲያጋጥሙ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ የቅርብ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ለሚመለከተው ሪፖርት መደረግ አለበት።

23. ልዩ ባህሪ ያላቸውን ዕቃዎች ስለመቆጣጠር

1) በመጋዘን የተቀመጡ አንዳንድ ለሕዝብ ጤና አደገኛ የሆኑ ዕቃዎች ወይም ጉዳትን የሚያስከትሉ የጦር መሣሪያዎች፣ መድኃኒቶች፣ ኬሚካሎች እና የመሳሰሉት ካላቸው ልዩ ባህሪ አኳያ እንደአስፈላጊነቱ ድንገተኛ ቆጠራ መደረግ አለበት፣

2) ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው፣በቀላሉ ሊወሰዱ የሚችሉ ዕቃዎች እና በፍጥነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ዕቃዎች ድንገተኛ ቆጠራ ሊደረግባቸው ይገባል፣

3) የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ ጊዜ በላይ የልዩ እቃዎች ድንገተኛ ቆጠራ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፣ እና

4) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ኃላፊነት ለሌላ አግባብ ላለው ኃላፊ በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

ምዕራፍ ስድስት
የቋሚ ንብረት አስተዳደር

24. የቋሚ ንብረት አመዘጋገብ

regular operation of the Public Body, considering the lead time needed to receive ordered goods, storage capacity, and the time required to fulfill purchase orders. This shall be done by forecasting and ensuring timely availability of necessary inventory.

2. For chemicals and medicines that have expired or are nearing expiration but do not cause harm, close monitoring and control shall be conducted, and a report shall be prepared accordingly.

23. Control of Items with Special Characteristics

1. Some items stored in inventory that are hazardous to public health or cause damage-such as armaments, medicines, chemicals, and similar items with special characteristics-shall be subject to perpetual inventory counts as necessary.
2. Items requiring special protection, those that can easily picked up, or fast moving shall also be subject to perpetual inventory counts.
3. The head of the Public Body may order more than one perpetual inventory count for special items as deemed necessary.
4. When necessary, the head of the Public Body may delegate the responsibility assigned to him in this article to another Official.

CHAPTER SIX
FIXED ASSET MANAGEMENT

24. Fixed Asset Recording

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

1) የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች እንደየሥራ ባህሪ እና ስፋት የቋሚ ንብረት ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ሊኖሯቸው ይችላል፣

2) የመንግስት መስሪያ ቤቶች ቋሚ ንብረቶች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን የኤሌክትሮኒክ የመረጃ ስርዓትን በመጠቀም በተሟላ ሁኔታ መዝግበው የመያዝ፣የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው፣

3) በተጠቃሚ እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች ዝርዝር በኤሌክሮኒክ የመረጃ ስርዓት የተዘጋጀ ኮፒ ለተጠቃሚዎች እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት፣

4) ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር መሰጠት ያለበት ሲሆን፣ ይህ ቁጥር በቋሚ ንብረቱ ላይ መለጠፍ ወይም በማይለቅ ቀለም መፃፍ አለበት፣

5) የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ሥርዓትን በመጠቀም የቋሚ ንብረት ካርዶች እና የቋሚ ንብረት ሠነዶች ወቅታዊ መደረጋቸውን መረጋገጥ አለበት፣

6) የቋሚ ንብረቶቹ ያሉበት የሚገኙበት ይዞታ ወይም የሚገኙበት ቦታ ላይ ማናቸውም ለውጥ ቢኖር በኤሌክሮኒክ የመረጃ ስርዓት ምዝገባው ላይ እንዲስተካከል መደረግ አለበት፣

7) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቱ ያከናወናቸውን የግንባታ ሥራዎች እንደ ቋሚ ንብረት በኤሌክትሮኒክ ስርዓት መመዝገብ አለባቸው፣

8) ልዩ ቋሚ ንብረቶች ለብክነት ሊዳረጉ ስለሚችሉ በኤሌክትሮኒክ መረጃ ስርዓት ተመዝግበው የገቢ እና ወጪ እንቅስቃሴያቸው ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል።

9) ቋሚ ንብረት ለአንድ የሥራ ክፍል ወይም ሠራተኛ ወጪ ሆኖ ከተሰጠ በኋላ ወደ መጋዘን ሣይመለስ በዚያው ወደሌላ ሠራተኛ ወይም የሥራ ክፍል በርክክብ ከተላለፈ

1. Public Bodies should have fixed asset custodians according to the nature and size of their operations.
2. From the time fixed assets are acquired, Public Bodies are responsible for fully recording, monitoring, and controlling the assets using the electronic data management system.
3. A copy of the detailed list of fixed assets held by users shall be prepared electronically and made available to the users.
4. Each fixed asset hall be assigned a unique identification number, which should be affixed to the asset either by engraving or by marking with indelible paint.
5. Public Bodies shall regularly verify the timeliness and accuracy of fixed asset cards and related documents using the electronic data management system.
6. Any changes in the location or custody of fixed assets shall be updated in the electronic data management system records.
7. Construction works carried out by the Federal Government Public Body shall be recorded electronically as fixed assets.
8. Special Fixed assets, which may be subject to loss, must be recorded in the electronic data management system and their movement shall be monitored.
9. Once fixed assets are issued to a unit or an employee, if transferred to another employee or

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ዝውውሩን ተከትሎ የኤሌክትሮኒክ ምዝገባው እንዲስተካከል መደረግ አለበት፣

10) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የንብረት አሰተዳደር ሥርዓትን ለማዘመን እና ያላቸውን ሀብት በዋጋና በመጠን ለማወቅ እንደ አስፈላጊነቱ አጠቃላይ የቋሚ ንብረት ቆጠራ በማድረግ መዝግበው መያዝ ይችላሉ።

25. የቋሚ ንብረቶች ዋጋ አተማመን

1) የተገዙ ንብረቶች የመጀመሪያ ዋጋ የሚረጋገጠው ንብረቱ ገቢ ሲሆን በተመዘገበበት ደረሰኝ ዋጋ መሠረት ነው፣

2) በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተገዛው ንብረት ዋናው ደረሰኝ በማይገኝበት ጊዜ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የመጀመሪያውን ዋጋ የሚገምቱት ተመሳሳይ ወይም አንድ ዓይነት ንብረቶች በተመሳሳይ ጊዜ የተገዙበትን ዋና ደረሰኝ መሠረት በማድረግ ይሆናል፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው ካልተገኙ የንብረቱን ዋጋ በግምት ይወሰናል።

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚተመነው የቋሚ ንብረት ዋጋ ለመሸጥ ወይም ለመተካት ጥቅም ላይ አይውልም።

26. ዋጋቸው የማይታወቅ ቋሚ ንብረቶችን ዋጋ ስለመተመን

ዋጋቸው የማይታወቅ ቋሚ ንብረቶችን በተመለከተ ከዚህ በታች የተመላከቱትን ድንጋጌዎች በመጠቀም ዋጋቸው መተመን አለበት፤

1) የተሽከርካሪ ዋጋ የሚተመነው አዲስ የመተኪያ ዋጋን መነሻ በማድረግ በሚመለከተው አካል

unit, the transfer shall be properly documented and reflected in the electronic records.

10. Public Bodies may conduct an initial comprehensive fixed asset count and keep registry as needed to modernise their property management system and to know the value and quantity of their assets.

25. Valuation of Fixed Assets

1. The initial cost of purchased assets is verified based on the acquisition cost recorded in the delivery receipt.
2. Without prejudice to sub-Article 1 of this Article, if the main delivery receipt for the purchased asset is not available, Public Bodies shall estimate the initial cost based on the delivery receipt of similar or the same type of assets purchased at approximately the same time.
3. If the conditions described in sub-articles 1 and 2 of this Article are not met, the value of the asset shall be determined by estimation.
4. The estimated value of fixed assets based on this article shall not be used for sale or replacing purposes.

26. Valuation of Other Fixed Assets without a Purchase Price

For fixed assets with unknown value, their value shall be determined in accordance with the provisions set forth below.

1. The value of vehicles shall be determined based on their new replacement value, using the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

የተዘጋጀውን ቀመር መሠረት አድርጎ በመጠቀም ይሆናል፤፤

2) የቢሮ ዕቃ ዋጋ የሚተመነው ዕቃው ያለበትን ይዞታ መሠረት ባደረገ መልኩ ይሆናል፤

3) የማሽነሪ፣ ቁሳቁስና ተገጣጣሚዎች፣ ወታደራዊ መገልገያዎችና ተመሳሳይ መሣሪያዎች ዋጋ የሚተመነው በነዚህ መሣሪያዎቹን የአገልግሎት ዘመን በመስፈርትነት በመውሰድ ሲሆን ስሌቱ በየዓመቱ የመሣሪያዎቹን አስር በመቶ የዋጋ ቅናሽ በማድረግ የሚሰላ ይሆናል፤

4) የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ ወይም ሙሉ በሙሉ የተበላሹ ቋሚ ንብረቶች በመዝገብ ዋጋቸው ይመዘገባሉ።።

27. የግንባታ ዋጋ አተማመን

1) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ህንፃዎችን ለመስራት የተደረገን የቅድመ ግንባታ ቀጥተኛ ወጪዎች፣ የአስተዳደርና ምክር አገልግሎት እና የመሣሰሉትን ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች አጠቃሎ የህንፃው ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፤

2) በግንባታ ላይ የሚገኙ ሥራዎች የሚተመኑት የተጠናቀቁትን ሥራዎች የምህንድስና ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል፤

3) ለሕንፃው የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው የሕንፃው የግንባታ ሥራ ካለቀ በኋላ ሕንፃውን ለመሥራት ወይም ለመግዛት የተደረገውን ጠቅላላ ወጪ በመነሻነት በመውሰድ ከዚሁ ሂሣብ ላይ በየዓመቱ አምስት በመቶ (5%) በመቀነስ ይሆናል።።

4) ሕንፃውን ለመሥራት ወይም ለመግዛት የተደረገው ጠቅላላ ወጪ የማይታወቅ ከሆነ የሕንፃው ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ እንደመነሻ ይወሰዳል፤

depreciation formula prepared by the relevant body.

2. The value of office equipment shall be determined based on their current condition.

3. The value of machinery, goods and their accessories, military equipments and other simiar equipments shall be estimated based on their useful service life, applying a 10% annual depreciation rate.

4. Fixed assets whose service life has ended or that are fully consumed shall be recorded in the books at their book value.

27. Valuation of Construction Works

1. The cost of a building shall include direct pre-construction costs, administrative and consultancy service costs, and other indirect expenses incurred in the construction of Federal Government buildings.

2. The valuation of construction works in progress shall be based on the engineering estimated value of the completed works.

3. The depreciation value of the building is calculated starting from the completion of the construction work, based on the initial total cost incurred for construction or purchase, depreciated annually at a rate of 5%.

4. If the total cost incurred for the construction or purchase of the building is unknown, the current

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

5) ሕንፃዎችን በሽያጭ ማስወገድ ሲፈለግ እንደቅደም ተከተላቸው የሚከተሉትን ዘዴዎች በመጠቀም የሕንፃውን ዋጋ መተመን ይቻላል፡ -

ሀ/ **የወቅታዊ ገበያ አተማመን ዘዴ፡-** ሕንፃው በግልፅ ጨረታ ቢሸጥ የሚኖረውን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ የሕንፃው ዋጋ ላይ መድረስ፣

ለ/ **በወቅቱ የመተኪያ ዋጋ ዘዴ፡-** የሕንፃው ትክክለኛ ዋጋ የማይታወቅ ከሆነ በአሁኑ ጊዜ የተመሣሣይ ሕንፃ አጠቃላይ የግንባታ የመተኪያ ወጪን ግምት ውስጥ በማስገባት መገመት ይቻላል። ይህ ማለት ተመሣሣይ ሕንፃ በተመሣሣይ አካባቢና በተመሣሣይ ዕቃ አሁን ለመሥራት ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ በማሰብ መከናወን ይኖርበታል፣

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከተው ቢኖርም፣ ጉዳዩ የሚመለከተውን የመንግሥት መሥሪያ ቤት በየጊዜው የሚያዘጋጀውን ግምታዊ ደረጃና የካሬ ዋጋ ወጪን መሠረት ባደረገ መስፈርት ተጠቅሞ የሕንፃዎቹን ዋጋ ማውጣት ይቻላል፣

7) የግምት ሥራን ለማከናወን የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ ሥራውን ለማከናወን የሚችሉ በቂ ባለሙያዎች የሌሉት እንደሆነ ሥራው ለሦስተኛ ወገን በመስጠት የሕንፃውን ዋጋ ማስላት ይቻላል።

28. በግንባታ ላይ ያሉ ቋሚ ንብረቶች

1) በግንባታ ላይ ያሉ ቋሚ ንብረቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት ግንባታቸው አልቆ ለተጠቃሚ ክፍሎች ርክክብ ከተፈፀመ በኋላ ነው።

2) የንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል በግንባታ ላይ* ያሉ ቋሚ ንብረቶችን የመከታተል ኃላፊነት አለበት።

market replacement cost of the building shall be considered as the initial cost.

5. When buildings are disposed of by selling, their value may be determined using one of the following methods:

a) **Current Market Valuation Method:** The building's value is determined based on the prevailing market price by assuming it will be sold through an auction.

b) **Current Replacement Cost Method:** If the exact value of the building is unknown, the estimated total replacement cost of a similar building in a similar location with similar construction inputs is used.

6. Notwithstanding sub-article 6 of this Articles, the Public Body may determine the value of buildings based on the estimated level and square meter cost prepared periodically by the relevant Public Body.

7. If the Public Body lacks sufficient experts to carry out the valuation, the work may be outsourced to a third party to estimate the building's value.

28. Fixed Assets under Construction

1. Fixed assets under construction can only be put into use after the construction is completed and handover to the user departments is properly conducted.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

3) የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በግንባታ ላይ ያሉ ቋሚ ንብረቶችን ለመቆጣጠር እንዲረዳቸው በግንባታ ላይ ያሉ ቋሚ ንብረቶች ማጠቃለያ ሰንጠረዥ መጠቀም አለባቸው።

29. የቋሚ ንብረት የእርጅና ቅናሽ

1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በየዓመቱ መጨረሻ ላይ የቋሚ ንብረት የእርጅና ቅናሽን በማስላት የንብረቱን የመዝገብ ዋጋ መመዝገብ አለባቸው፣
2) የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴን በመጠቀም ነው።
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች ሌሎች የእርጅና አቀናነስ ዘዴዎችን መጠቀም የሚቻለው ሚኒስቴሩ ሲፈቅድ ብቻ ነው።።
4) የቋሚ ንብረት የእርጅና ቅናሽን የማስላትና በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የመመዝገብ ኃላፊነት የእያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውን የሥራ ክፍል ይሆናል።
5) በበጀት ዓመቱ መካከል ለተገዙ ቋሚ ንብረቶች የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው ንብረቱ ወደ መጋዘን ገቢ ከሆነበት ዕለት ጀምሮ ይሆናል፣
6) በመንግሥት ቋሚ ንብረት ላይ የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው የንብረቱን ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ሣይሆን ተገቢ እና ሚዛናዊ ዋጋ ላይ ለመድረስ ነው። የቋሚ ንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ የሚታወቀው ሲሸጥ በሚገኝ የገበያ ዋጋ ብቻ ይሆናል።

2. The property administration unit is accountable for monitoring fixed assets under construction.
3. Public Bodies must use a summary schedule of fixed assets under construction to assist in controlling these assets.

29. Depreciation of Fixed Assets

1. Public Bodies must record the depreciation of fixed assets at the end of each fiscal year and shall updating the book value of the asset accordingly.
2. Depreciation is calculated using the straight-line depreciation method.
3. Without prejudice to sub-article 2 of this Article, Public Bodies may use other depreciation methods only if approved by the Ministry of Finance.
4. The responsibility for calculating and recording fixed asset depreciation in the electronic system lies with the property administration unit of each Public Body.
5. Depreciation for fixed assets purchased during the fiscal year begins from the date the asset is received by the warehouse unit.
6. Depreciation on government fixed assets is intended to determine the appropriate and proportional value of the asset, not to determine its actual value. The value of a

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

7) በቋሚ ንብረት ላይ ያለ የመዝገብ ዋጋ ንብረትን ለማስወገድ መነሻ፣ የጨረታ መነሻ እና የጠፋ ንብረት መተኪያ ዋጋ ግምት ሆኖ ሊወሰድ ይችልም፡፡

8) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ አባሪ 5 የተመለከተውን የቋሚ ንብረት እርጅና ቅናሽ ተመን ተከትለው ማስላት ይችላሉ፡፡

9) በንዑስ አንቀፅ 8 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ላይ የእርጅና ቅናሽን በተመለከተ በተቀመጠው አግባብ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

30. የቋሚ ንብረት አጠቃቀምና ጥገና

1) ለማሽነሪዎች/መሣሪያዎች፣ለተሽከርካሪዎች፣ ሕንፃዎችና ለሌሎች ንብረቶች መሠረታዊ ጥገና የተደረገላቸው ንብረቶች ሲሆኑ የሚኖራቸውን የአገልግሎት ዘመን ያራዝማል ተብሎ ሲታመን ብቻ ወጪው አስቀድሞ በቋሚ ንብረት በተመዘገበው ሂሳብ ላይ ተደምሮ መመዝገብ አለበት፡፡

2) ማንኛውም የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ለተሽከርካሪዎች፣ ህንፃዎች፣ ኮምፒውተሮች እና ሌሎች መሳሪያዎች በስራ ላይ ባሉበት ወቅት ለሚያጋጥሙ ወይም ለሚታዩ ብልሽቶች የድህረ ብልሽት ጥገና የሚያገኙበትን ይወስናል፡፡

3) ጥገና ያገኘው ተሽከርካሪ፣ ማሽን፣ ህንፃና ሌሎች ንብረቶች ለስንት ጊዜ ጥገና እንደተደረገላቸው እና

fixed asset shall be determined by its market value when it will be sold.

7. The book value of fixed assets shall not be used as a basis for disposal, starting auction price, or estimated value of lost assets.

8. For the implementation of this article, Public Bodies may follow the fixed asset depreciation schedule attached in Annex 5 of this Directive.

9. Without prejudice to the provisions of Sub-Article 8, the provisions of Income Tax Regulation No. 410/2009 (as ameded) concerning depreciation deductions shall apply.

30. Utilizatio and Maintenance of Fixed Assets

1. For machinery/equipment, vehicles, buildings, and other properties that have undergone basic maintenance, it is considered that their service life is extended. Upon this assumption, the expense shall be recorded in advance in the fixed asset account where the property is registered.

2. Any Public Body shall schedule and carry out preventive and corrective maintenance for vehicles, buildings, computers, and other equipment for defects observed while providing services within a specified time frame.

3. For vehicles, machinery, buildings, and other properties that undertake maintenance, the number of times maintenance has been performed, the type of maintenance, the cost, and

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

የጥገናው ዓይነት፣ ወጪ እና ድግግሞሽ በንብረቱ የህይወት ታሪክ ላይ ተመዝግቦ መያዝ አለበት።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተመዝግበው የተያዙ እና በተደጋጋሚ ጥገና የሚደረግላቸው ቋሚ ንብረቶች ከሚሰጡት አገልግሎት በላይ ወጪን የሚጠይቁ በሚሆኑበት ጊዜ ንብረቶቹ ተለይተው ተገቢው ወሳኔ እንዲሰጥባቸው መደረግ አለበት።

31. በእርዳታ ወይም በስጦታ ወይም በዝውውር የተገኙ ንብረቶች

1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በእርዳታ፣ በስጦታ ወይም በዝውውር እና ከሌሎች ምንጮች የሚያገኙዋቸውን ንብረቶች ሲረከቡ የሚከተሉትን ሁኔታ በመከተል ብቻ መሆን አለበት፤

ሀ/ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ዕውቅና የተሰጣቸው፣

ለ/ ለፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ ገቢ ከተደረጉ በኋላ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ፣

ሐ/ የአገልግሎት ዘመናቸውን ያልጨረሱ፣

መ/ ከንብረቶቹ አገልግሎት አንፃር የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱን ከፍተኛ ማስወገጃ ወጪ የማይዳርጉ፣

ሠ/ የሥራ ማስኬጃ ወጪያቸው ከሌሎች የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ ንብረቶች አንፃር የተለየ ሊሆን አይገባም፣ እና

ረ/ የተለያዩ ዓይነት ኬሚካሎች፣ የላቦራቶሪ ሬኤጀንቶች እና ሌሎች በጤና እና አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ዕቃዎችን በተመለከተ

the frequency must be recorded and maintained in the asset's life history.

4. Subject to subsection 3 of this article, for fixed assets that are registered and repeatedly maintained, if the maintenance cost exceeds the service provided, the assets should be separated and an appropriate decision shall be made.

31. Properties Acquired by Grant, Donation, or Transfer

1. Public Bodies, when receiving properties through grant, donation, transfer, or from other sources, shall adhere only to the following conditions:
   a) The properties shall be entrusted by the head of the Public Body.
   b) The properties shall be capable of providing the appropriate service to the Public Body
   c) The service life of the properties not yet completed
   d) No excessive cost shall occur on the public body for disposal due to a long service year of the properties.
   e) Their operating and maintenance costs should not be significantly different as compared with other properties of the Public Body.
   f) For chemicals, laboratory reagents, and other items that may cause health and environmental damage, authorization to be

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል ዕውቅና ሊሰጥባቸው ይገባል።

2) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በእርዳታ፣ በስጦታ ወይም በዝውውር እና ከሌሎች ምንጮች የሚያገኙዋቸውን ንብረቶች ምንጫቸው ከየት እንደሆነ በተጨማሪም ዋጋንና የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚገልፅ መረጃ ከለጋሾች ወይም በስጦታ ንብረቱን ካስተላለፉት አካላት የጽሁፍ መረጃ መቅረብ አለበት።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት መረጃው መቅረብ ካልቻለ ከሌሎች ከሚመለከታቸው ምንጮች እና የመንግስት ተቋማትን በመጠየቅ አስፈላጊዎቹ ሰነዶች እንዲሟላ መደረግ አለበት።

32. በትውስት ስለሚገኙ ንብረቶች

1) በትውስት የተገኙ ንብረቶች ዋጋ እና የአገልግሎት ዘመናቸውን ከንብረቱ ባለቤቶች የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የቋሚ ንብረቶች መዝገብ ላይ መመዝገብ አለባቸው።

2) በትውስት የተገኘው ንብረት ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ በግልፅ ሊቀመጥና ጊዜው እንደተጠናቀቀም ንብረቱን በትውስት ለሰጠው አካል መመለስ አለበት፣

3) በትውስት የተገኘ ንብረት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ወጪ ንብረቱን በትውስት ባገኘው የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት መሸፈን አለበት፣

4) ንብረቱን በትውስት በሰጠው የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት በኩል በትውስት ከዛደበት ቀን ጀምሮ በንብረቱ ስም ምንም ዓይነት ወጪ መፈጸም የለበትም።

given by the designated government body is a precondition before receiving them.

2. Public Bodies shall receive written documentation from donors or transferring bodies that clearly states the source, value, and service life of properties acquired by grant, donation, transfer, or from other sources.
3. If it is not possible to provide the documentation mentioned in sub-Article (2) of this Article, the office shall obtain the necessary documents by consulting other relevant sources and government bodies to complete the required information.

32. Properties Acquired through Loan

1. The value and service life of properties acquired through loan must be recorded in the fixed assets register using the electronic system, based on information obtained from the owners of the property.
2. It shall be clearly stated how long the borrowed property will be held, and once the loan period is completed, the property shall be returned to the lending entity.
3. Any expenses incurred on the borrowed property must be borne by the borrowing office.
4. From the date the property is borrwed out, the lending office shall not incur any expenses under the name of the property.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ምዕራፍ ሰባት
የመንግሥት ንብረት ማስወገድ

ክፍል አንድ
ንብረትን የማስወገድ ጠቅላላ ድንጋጌ

33. ንብረትን የማስወገድ ሥርዓት

ማንኛውም የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ንብረትን ሊያስወግድ የሚችለው በዚህ የመመሪያው ምዕራፍ እና በአዋጁ የተደነገጉትን መሠረታዊ መርሆች እና የአሰራር ሥርዓቶችን በመከተል ብቻ ነው።

34. ንብረትን የማስወገድ ሂደት

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ንብረቶችን ለማስወገድ የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ይኖርባቸዋል፡

1) የንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል ዓመታዊ የንብረት ቆጠራን እና ሌሎች መነሻዎችን መሠረት በማድረግ የሚወገዱ ንብረቶችን ዝረዝር እና የማስወገጃ ዘዴዎቹን በመምረጥ ለመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት።

2) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገውን መሰረት በማድረግ የቀረቡትን የሚወገዱ ንብረቶች የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሽያጭ ከሚወገድ ንብረቶች ውጪ የሆኑትን መርምሮ በማጽደቅ ለንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል ይመራል።

3) የንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል እንዲወገዱ የተመሩለትን ንብረቶች መርምሮ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የተደነገገውን የንብረት

CHAPTER SEVEN
DISPOSAL OF GOVERNMENT PROPERTY
SECTION ONE
GENERAL PROVISIONS OF PROPERTY DISPOSAL

33. Property Disposal Procedure

Any Public Body may dispose of property only by following the fundamental principles and procedures outlined under this chapter and as stipulated on the proclamation.

34. Property Disposal Process

Public Bodies must follow the following procedures to dispose of properties:

1. Based on the annual property inventory and other initial data, the property administration unit shall timely submit to the head of the Public Body, a proposal listing of the properties to be disposed of and the methods of their disposal.
2. The head of the public body shall review and approve assets to be disposed of—other than those subject to sale—in accordance with the provisions of Sub-Article 1 of this Article, and shall forward them to the Property Administration Unit.
3. The Property Administration Unit shall examine the selected properties and dispose them by following the property disposal procedures

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ማስወገድ ሂደት በመከተል ንብረቱ እንዲወገድ ያደርጋል፤

4) በሽያጭ የሚወገዱ ንብረቶች ውጤትን ሳይጨምር የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ከንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል የቀረበለትን የውሣኔ ሃሳብ ያፀድቃል፤

5) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመሥሪያ ቤታቸው በተለያዩ ጊዜያት የተከማቹ ንብረቶችን ጊዜያቸውን ጠብቀው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተደነገገውን የአወጋገድ ሥርዓት ተከትለው በወቅቱ እንዲወገዱ ማድረግ አለባቸው

35. የንብረት ማስወገድ ሥርዓቶች

1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የመንግሥት ንብረት እንዲወገድ ለምን እንዳስፈለገ ለይተው የማወቅ ኃላፊነት አለባቸው::

2) የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲወገድ የተለየውን ንብረት በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለባቸው፤

ሀ/ በጨረታ የተወገዱ ንብረቶች ለአሸናፊ ድርጅት ወይም ግለሰብ ርክክብ ሲደረግ አግባብ ባለው የንብረት ወጪ ሰነድ በመጠቀም ማስረከብ፤

ለ/ በመቅበር፣ በማቃጠል፣በማምከን፣ በማፈን እና በመቀየጥ የተወገዱ ንብረቶች ለማስረጃነት እንዲያገለግል ንብረት የሚያስወግደው አካል የተወገዱት ንብረቶች ዝርዝር እና የአፈጻጸም ቃለ ጉባኤው የንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል ሊደርሰው ይገባል:: በቀረበው *ዝርዝር

stipulated in the Proclamation and in this directive.

4. For properties to be disposed of by sale, the head of the Public Body shall approve the disposal proposal submitted by the Property Administration Unit, excluding the decision to determine the the result of the Auction.

5. Public Bodies must monitor the disposable properties accumulated in their premises to dispose them timely by following the disposal procedures stipulated in the proclamation and in this directive.

35. Property Disposal Procedures

1. Public Bodies have the responsibility to clearly identify the reasons why a government property needs to be disposed of.

2. Regarding the specific property to be disposed of, Public Bodies shall carry out the following actions:

   a) For properties disposed of by auction, when transferring ownership to the winning enterprise or individual, proper documentation of property disposal costs must be used.

   b) Properties disposed of by nutralizing, burning, burial, melting, or alteration must be documented. The disposing public Body shall prepare a detailed list of the disposed properties and submit it along with the minutes to the property administration unit.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

መሠረትም ንብረቶቹ ከንብረት መዝገብ መሰረዝ አለባቸው።

36. የተሽከርካሪ እና ልዩ ልዩ ማሽነሪ ማስወገጃ መስፈርቶች

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተሽከርካሪን እና ልዩ ልዩ ማሽነሪ ለማስወገድ ከሚከተሉት መመዘኛ ቢያንስ አንዱ መሟላቱን ማረጋገጥ አለባቸው።

1) በከፍተኛ ጉዳት ምክንያት ሊጠገን የማይችል ሲሆን፣
2) የመለዋወጫ ዕቃው በገበያ ላይ አለመገኘት፣
3) ለማደስ የሚያስፈልገው ወጪ ከመተኪያ ዋጋው ጋር ሲነፃፀር መተካቱ የሚመረጥ ሲሆን፣
4) በቴክኖሎጂ ኋላቀርነት ምክንያት ምርታማነቱ ዝቅተኛ ሲሆን፣
5) መሥሪያ ቤቱ ከሚኖረው ወቅታዊም ሆነ የቅርብ ጊዜ የሥራ ዕቅድ አንፃር ትርፍ መሆኑ ሲታመን፣
6) አገልግሎት በሰጠባቸው ጊዜያት ለጥገና እና ለነዳጅ የወጣው ጠቅላላ ወጪ ከሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ ሳይሆን ሲቀር፣
7) በእርጅና ምክንያት አገልግሎት መስጠት የማይችል ሲሆን እና ሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ሲያጋጥሙ።

ክፍል ሁለት
ንብረትን በሽያጭ ስለማስወገድ

37. ንብረትን በሽያጭ የማስወገድ ሥልጣን

Based on this list, the properties must be removed from the fixed asset register.

36. Disposal Criteria for Vehicles and Special Machinery

Public Bodies must ensure that at least one of the following criteria is met before disposing of vehicles and special machinery:

1) The item is irreparable due to severe damage.
2) Its Spareparts is not available in the market.
3) The cost of repairing the item exceeds or is close to the purchase price, making repair uneconomical.
4) The productivity of the item is low due to technological obsolescence.
5) The Public Body believes that, based on current or near-future work plans, the item is no longer useful.
6) The total expenses incurred for maintenance and fuel during the service period are disproportionate to the service provided.
7) The item is incapable of providing service due to wear and tear or other similar reasons.

SECTION TWO
DISPOSAL OF PROPERTY BY SELLING

37. Power to Disposal of Property by Salling

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

1) ንብረቱን ለማስወገድ የተገመተው የመነሻ ነጠላ ዋጋ እስከ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) እና በጥቅል ዋጋ እስከ ብር 2,000,000/ሁለት ሚሊዮን ብር/ በሚሆንበት ጊዜ ንብረቱን በሚያስተዳድረው መሥሪያ ቤት እንዲወገድ ይደረጋል፣

2) የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሽያጭ እንዲወገዱ የሚፈልጓቸውን የነጠላ ዋጋ ግምታቸው ከብር 50,000/ሃምሳ ሺህ ብር/ በላይ የሆኑ እንዲሁም የጥቅል ዋጋ ግምታቸው ከብር 2,000,000 /ሁለት ሚሊዮን ብር/ በላይ የሆኑ ንብረቶችን በመለየት በአዋጁ አንቀጽ 59 (1) መሠረት በየጊዜው ዝርዝር መረጃ በማዕከል ግዥን ለመፈጸምና ንብረትን ለማስወገድ ለተቋቋመው ለፌደራል የመንግሥት ግዥ አገልግሎት መስሪያ ቤት በመላክ እንዲወገዱ ይደረጋሉ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቶች በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ የሚያስወግዷቸውን ነጣጥለው ሊያቀርቡ አይገባም።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ባለስልጣኑ በማዕከል የሚወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር በየጊዜው የሚወስናቸውን ጨምሮ በልዩ ሁኔታ በባለስልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር የመንግሥት መስሪያ ቤት በራሱ ተሽከርካሪን፣ የተሽከርካሪ አካላትን እና መለዋወጫን በሽያጭ ማስወገድ አይችልም።

5) ማንኛውም የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤት ተሽከርካሪ በሽያጭ ለማስወገድ ሲወስን አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃን በማሟላት ተሽከርካሪን በማዕከል እንዲያስወገድ ሥልጣን ለተሠጠው ለመንግስት ግዥ አገልግሎት መስሪያ ቤት በማቅረብ እንዲወገድለት ማድረግ አለበት፤

1. If the unit estimated starting value of the property to be disposed of is birr 50,000 (fifty thousand) or less and its total estimated value is not exceeding birr 2,000,000 (two million), it shall be disposed of by the respective Public Body.

2. The Public body shall identify assets intended for disposal through sale that have an individual value exceeding Birr 50,000 (fifty thousand Birr) and a total value exceeding Birr 2,000,000 (two million Birr), and shall periodically submit detailed information to the Federal Government Procurement Service, which is responsible for conducting centralized procurement and asset disposal in accordance with Article 59(1) of the Proclamation.

3. Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1 of this Article, Government Offices shall not submit for disposal all assets intended for disposal within a single fiscal year.

4. Notwithstanding the provisions of Sub-Article 1 of this Article, a Government Office shall not dispose of vehicles, vehicle components, or spare parts through sale—except in special cases as determined by the Authority, including where the items are listed for centralized disposal—unless expressly authorized by the Authority.

5. When a Federal Government Office decides to dispose of a vehicle by sale, it shall submit the required documentation to the Government Procurement Service Office, which is mandated to carry out centralized vehicle disposal.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

6) በአዋጅ አንጽ 45 (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚወገደው ንብረት ቀደም ብሎ ያልተከፈለ ዕዳ ካለበት የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤቱ የመሸፈን ኃላፊነት የለበትም። እንዲወገድ የቀረበው ንብረት ያልተከፈለ ዕዳ ያለበት ከሆነ የመንግስት መሥሪያ ቤቱ የሚሸጠው ንብረት ላይ ያሉትን ዕዳ እና ተጠያቂነቶች ለይቶ የማወቅ እና ይህንንም ለሽያጭ ጨረታው ተሳታፊ በጨረታ ሰነዱ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 6 የተደነገገው ቢኖርም ከቀረጥና ታክስ ውጭ ያሉ እና ያልተከፈሉ የቦሎ እና ሌሎች ተያያዥ ወጪን የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤቱ የመክፈል ኃላፊነት አለበት።

8) በዚህ አንቀጽ የተደነገገውን ለመፈፀም እንዲቻል የባለድርሻ አካላት በተለይም የጉምሩክ ኮሚሽን እና የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ወይም የትራንስፖርት መ/ቤቶች የተሸከርካሪን የቀረጥና ታክስ እንዲሁም ተያያዥ ዕዳ በወቅቱ ማሳወቅ አለባቸው።

38. ንብረትን በሽያጭ የማስወገድ አፈፃፀም

1) የመንግስት መ/ቤቶች ንብረትን በሽያጭ እንዲወገድ በሚወስኑበት ጊዜ የኤሌክትሮኒክ የንብረት ሽያጭ ሥርዓትን መጠቀም አለባቸው፣

2) የመንግስት ንብረትን በሽያጭ ለማስወገድ በሚወጣ ጨረታ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ወይም በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የተቋቋመ የንግድ ደርጅት ሊሳተፍ ይችላል፣

6. Subject to the provisions of Article 45(1) of the Proclamation, a Federal Government Office shall not assume liability for any outstanding debt associated with a property being disposed of. If the property to be disposed of is encumbered, the Government Office shall identify such liabilities and explicitly disclose them in the bidding documents for the sale.

7. Notwithstanding the provisions of Sub-Article 6 of this Article, the Public Body shall remain responsible for paying non-taxable and non-duty-related expenses, such as BOLO and other relted fees that remain unpaid.

8. To implement the provisions of this Article, relevant stakeholders—particularly the Customs Commission and the Driver and Vehicle Licensing and Control Authority or other transport agencies—shall promptly provide information on vehicle-related taxes, duties, and outstanding liabilities.

38. Implementation of Property Disposal by Sale

1. When deciding to dispose of property through sale, Public Bodies shall utilize the electronic government property disposal system.

2. Any Ethiopian national or business entity established under Ethiopian law shall be eligible to participate in auctions for the disposal of government property.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

3) የመንግስት መ/ቤቶች ንብረትን በሽያጭ እንዲወገድ በሚወስኑበት ጊዜ ባለስልጣኑ ያዘጋጀውን የመንግስት ንብረትን በሽያጭ ለማስወገድ የሚውል መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀም አለባቸው፤

4) የንብረት ሽያጭ ጨረታ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመከተል እስከወጣ ድረስ የመደበኛ ጨረታ ሠነዱ ላይ መፈረም ሳያስፈልግ ሰነዱ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

5) ንብረትን በሽያጭ የሚያስወግደው የመንግስት መስሪያ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ለጨረታ ሰነዱ ከብር ሁለት መቶ ያላነሰ እና ከብር አምስት መቶ ያልበለጠ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል::

6) ከላይ በንዑስ አንቀፅ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዕከል የሚሸጡ ንብረቶች ሲሆኑ ከብር አምስት መቶ ያላነሰ እና ከብር ሁለት ሺህ ያልበለጠ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል::

7) ሚኒስቴሩ ለባለስልጣኑ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን የመጠቀም እና ተያያዥ ችግር ሲገጥማቸው ከኤለክትሮኒክ ሥርዓት ውጭ ሽያጭ መፈፀም የሚችሉት ጥያቄያቸውን ለባለስልጣኑ አቅርበው ሲፈቀድላቸው ብቻ ነው፤

3. Public Bodies shall use the standard bidding document for the disposal of government property, as prepared and issued by the Authority, when disposing of property through sale.

4. Where property sales are conducted via the electronic bidding system, the submission of a bid shall be deemed valid without the requirement to sign the conventional bid document.

5. A Public Body conducting a property sale may charge a fee for the bid document, which shall not be less than two hundred Birr and not more than five hundred Birr, as appropriate.

6. Subject to Sub-Article 4 of this Article, where the property is disposed of through centralized sales, a bid document fee of not less than five hundred Birr and not more than two thousand Birr may be charged.

7. In accordance with the delegation granted by the Ministry to the Authority, Public Bodies may, where they face operational difficulties in using the electronic disposal system, request and obtain approval from the Authority to conduct the sale using alternative procedures outside the electronic system.

39. በኤሌክትሮኒክ ግልጽ ጨረታ ወይም በሀራጅ በመሸጥ ስለማስወገድ

የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የመንግሥት ንብረት በኤሌክትሮኒክ ጨረታ ወይም በሀራጅ ለመሸጥ ሲወስኑ

39. Disposal by Electronic open bid or Auction

Public Bodies, when deciding to sell government property through electronic open bid or auction they must ensure that the following preconditions are met:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

ቀጥሎ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

1) የሚወገደው ንብረት በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቱ አገልግሎት መስጠት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፡፡
2) የሚወገዱት ንብረቶች በጨረታ ወይም በሀራጅ ለመሸጥ ዝርዝራቸው ለመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊው ቀርቦ መወሰኑን፣
3) ከሌሎች የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎች የተሻለ አማራጭ መሆኑ ሲረጋገጥ ፣
4) ሽያጩን ለማከናወን ያለውን አመችነትና ፍጥነት፣
5) ከግልጽ ጨረታና ከሀራጅ የመሸጫ ዘዴ የሚኖረውን ተጽዕኖ በመገምገም የተሻለውን መምረጥ፣
6) ንብረቶቹን በጥቅል በመሸጥ ጊዜን እና ወጪን መቀነስ ማስቻሉን፣
7) በጨረታ ወይም በሀራጅ ንብረቱን ለመሸጥ የተደረገው ጥረት ካልተሳካ ንብረቱ የሚወገድበትን ሌላ አማራጭ ዘዴ ለየመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊው ቀርቦ መወሰን አለበት፣
8) ንብረቱ ሁለት ጊዜ በኤሌክትሮኒክ ጨረታ ወጥቶ በመነሻ ዋጋ ካልተገኘ የመነሻ ግምት ዋጋ መከለስ አለበት፡፡
9) ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) በተገለጸው መሠረት ሽያጩ የማይሳካ ከሆነ በሶስተኛው ሽያጭ ጨረታ ሂደት በተገኘው ዋጋ መሸጥ ይቻላል፡፡

40. ኤሌክትሮኒክ የመንግስት ንብረት ሽያጭ የግንኙነት ዘዴ

1) It is confirmed that the property to be disposed of can no longer provide service to the Public Body.
2) The detailed list of properties to be sold by open bid or auction is submitted to the head of the Public Body and approved.
3) It is confirmed that selling the properties through open bid or auction is a better option.
4) The convenience and speed to conduct the sale are ensured.
5) The sale method is selected after evaluating the pros and cons of the sales methods and by choosing the most advantageous one.
6) By ensuring that selling the properties in bulk reduces time and cost.
7) If the attempt to sell the property by open bid or auction fails, an alternative disposal method must be proposed to the head of the Public Body for decision.
8) If a property is auctioned twice through the electronic auction system without being sold at the initial starting price, the starting price shall be subject to revision.
9) Notwithstanding Sub-Article (8) of this Article, if the property remains unsold after two unsuccessful electronic auction attempts, it may be sold at the highest price offered during the third auction process.

40. Electronic Government Property Sale Communication Method

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

1) ከመንግስት ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የንብረት ሽያጭ ግንኙነት በኤሌክትሮኒክስ የመንግስት የንብረት ሽያጭ ስርዓት መሆን አለበት፡፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም ከንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ የንብረት ሽያጭ ግንኙነት ማለት የንብረት ማስወገድ እቅድ ይፋ ማድረግን፣ የጨረታ ማስታወቂያን የጨረታ ሽያጭ ሰነድን፣ማሻሻያና ማብራርያ አቀራረብን፣ የጨረታ መክፈቻ ስነ-ስርዓቶችን፣ የጨረታ ግምገማ ውጤትና አገላለጽ፣ አቤቱታ አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥና እንዲሁም በውል አሰተዳዳር ወቅት ያሉና ሌሎች ተያያዥ ግንኙነትን ያካትታል፡፡

41. ኤሌክትሮኒክ የንብረት ሽያጭ ማስታወቂያ ሂደት

1) የመንግስት መስሪያ ቤቶች ንብረትን በሽያጭ ለማስወገድ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም የጨረታ ማስታወቂያ ወይም ግብዣ በማድረግ እና በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ንብረት ማስወገድ ስርዓትን በመጠቀም የጨረታ ማስታወቂያውን ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

2) በአንድ ጊዜ በሽያጭ የሚወገደው ንብረት በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በኩል የሚፈፀም ሲሆን የጨረታ ማስታወቂያው ለ15 ተከታታይ ቀናት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ክፍት ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ አለበት፣

3) የሚሸጠው በማዕከል እንዲያስወገድ ሥልጣን ለተሠጠው በፌደራል መንግሥት ግዥ አገልግሎት መስሪያ ቤት በኩል የሚፈጸም ሲሆን የጨረታ ማስታወቂያው ከ20 ቀናት ያላነሰ ክፍት ሆኖ

1. Any communication related to the sale of government property must be conducted through the electronic government property sale system.
2. For the implementation of subsection (1) of this article, the communication method includes making the property disposal plan public, issuing auction announcements, preparing auction sale documents, providing amendments and clarifications, managing auction payment procedures, reporting auction evaluation results and feedback, complaint handling, and other related communications during contract administration.

41. Electronic Property Sale announcement Process

1. Public Bodies must use the electronic system to announce auctions or invitation when disposing of property by sale, and make the auction notification public through the government electronic property disposal system.
2. When a Property to be sold at once is to be conducted by a Public Body, the bidding announcement must be posted on the electronic system and shall remain open for 15 calendar days.
3. If the sale of government property is conducted centrally by the designated Federal Procurement Service, the sale notification must be publicly available for no less than 20 days on the

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 8th of July 2025.

የሚቆይበትና በኤሌክትሮኒክ ስርዓቱ ቢያንስ ለ1 ጊዜ ማስታወቂያው ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን መደረግ አለበት፣

4) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኤሌክትሮኒክ በሚያወጡት የጨረታ ማስታወቂያ ላይ ቢያንስ ቀጥሎ የተመለከቱትን ዝርዝሮች ማካተት አለባቸው፡፡

ሀ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ስምና አድራሻ፣
ለ/ የዕቃዎቹን ዓይነት፣ ዝርዝር፣
ሐ/ ዕቃዎቹ ለእይታ ክፍት ሆኖ የሚቆዩበትን ጊዜ እና ዕቃዎቹ የሚገኙበትን ቦታ፣
መ/ ተጫራቾች ዋጋ ሞልተው የሚልኩበት የጊዜ ገደብ፣
ሠ/ ጨረታው የሚዘጋበትና የሚከፈትበት ቀንና ሰዓት፣
ረ/ የጨረታ ማስከበሪያውን መጠን ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ከውድድሩ ቢወጡ የጨረታ ማስከበሪያው ለመንግሥት ገቢ እንደሚሆን መግለጽ፣
ሰ/ ክፍያው እንዲፈፀም የሚፈለግበት ጊዜ፣
ሸ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል ለመሠረዝ እንደሚችል መግለጽ፣

42. የሚወገዱ ንብረቶች የጨረታ ሥነ ሥርዓቶች

1) የንብረት አስተዳደር የስራ ክፍል በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው ቀንና ሰዓት መሠረት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ጨረታውን መዝጋትና መክፈት አለበት፣

2) ማንኛውም ተጫራች የጨረታ መክፈቻ የግል የሚስጥር ቁልፍ ማቅረብ በሚገባው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተጫራቾቹ በራሱ ፈቃድ ከጨረታው እንደወጣ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

electronic system, with at least one public announcement.

4. Public Bodies must include at least the following details in their electronic auction notification:
